**Ethiopian Sport & Culture Federation in Europe**
**በአውሮፓ የኢትዮጵያውያን የስፖርትና ባህል ፌዴሬሽን**

**ቀን:** 18/06/2013
**ቁጥር:** 076/ESCFE/2013

## ከአውሮፓ ፌድሬሽን የተሰጠ መግለጫ፤

በመጀመሪያ በአውሮፓ የኢትዮጲያውያን ስፖርትና ባህል ፌድሬሽን የከበረ ሰላምታውን እያቀረበ በመቀጠልም በመላው አውሮፓና ከዛም ባሻገር ኢትዮጲያውያን ህብረተሰባችንን በዓመት አንድ ጊዜ በስፖርትና ባህል ጥላ ስር የማሰባሰብ የፌድሬሽናችን ዋነኛ ተልዕኮ ከዓመት ወደ ዓመት እየገዘፈ የመጣ መሆኑ በየጊዜው የሚታዩት የጋራ ስራዎቻችን ምስክሮች ናቸው። ይህ የጋራችን የስራ ውጤት ከ8 ቡድኖች ወደ 18 ቀጥሎም እየጨመረ በመምጣት በዘንድሮ ውድድር በአንደኛና በሁለተኛ ዲቪዚዮን ስር 28 ቡድኖች ተመዝግበው ለመወዳደር በመጠባበቅ ላይ ይገኛሉ። ይህም የተወዳዳሪዎች ቁጥር መጨመር በሌላ መልኩ የሚያሳየው የታዳሚውንም ህብረተሰብ ብዛት መጠን እየጨመረ መምጣቱንም ጭምር ይሆናል። ይህም እሰየው የሚያሰኝና የሁላችንም የጋራ ጥረትና የመሰባሰብ ፍላጎት ውጤት ነውና ሁላችንም ልንደሰትበትና ልንኮራበት ይገባል። ይህም ሲባል ደግሞ በአንፃሩም በአካሄዳችን ላይ ብዙና የተለያዩ ችግሮችና ድክመቶች አይተናል፤ ተማምረናል፤ አሁንም በመታየት ላይ ይገኛል። በተለይም፤

- አብሮ የመስራት ልምድ ማነስ፤
- የብዙሃን ጥቅም ልምድ ማስጠበቅ ልምድ ማነስ፤
- የመወቃቀስና የመተራረም ልምድ ማነስ፤
- የመቻቻልና የመከባበር ልምድ ማነስ፤
- የተሰጠንን ሃላፊነት በተገቢው መልክ የመወጣት ልምድ ማነስን

የመሳሰሉት ድክመቶች ሲተገበሩና ሲንፀባረቁ በየጊዜው ይታያሉ። ምንም እንኳን በቡድን አመራርና በአባላቶች መካከል የሚከሰቱ ችግሮች ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየቀነሰ የመጣ ቢሆንም ነገር ግን ችግሮችን የመፍታት አቅም ካለመኖሩ የተነሳ በቀላሉ መታየት የሌለባቸውና በፌድሬሽኑ በኩል መፍትሄ የሚያስፈልጋቸው ለመሆኑ ከአጠቃላይ ጉባኤው በተደጋጋሚ ሲነገር ቆይቷል። ፌድሬሽኑም ቡድኖች የራሳቸው የውስጥ ሁኔታ በራሳቸው ለመፍታት የሚያደርጉትን ጥረት እስከዛሬ ድረስ በእጅጉ የደገፈና ለወደፊቱም የሚደግፍ ለመሆኑ እያረጋገጠ ነገር ግን ቡድኖች ችግራቸውን መፍታት ካልቻሉና አቤቱታ ከቀረበ ሁኔታዎችን በመከታተል መፍትሔ አዘል ዳኝነት መስጠት እንዳለበትም በዚሁ አጋጣሚ በጥብቅ ማሳሰብን ይወዳል፤ ከአባለቱም በተደጋጋሚ ተጠይቋል። ዘንድሮም በአመራር አካሎችና በቡድን አባሎች መካከል ችግሮች መፈጠራቸውን መላው የቦርድ አባላት የሚያውቁትና ምላሹንም በጉጉት የሚጠበቅ መሆኑ በግልፅ የሚታወቅ ነው።

ኢትዮ ክለን በመጀመሪያውና ታሪካዊው የፌድሬሽኑ ምስረታ ላይ በአቶ ጳውሎስ ተወካይነት ከተገኝበት ጊዜ ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ በፌድሬሽኑ ፌስተቫሎች ላይ በመገኘት ከፍተኛ አስተዋጾ ያደረገ አንጋፋ ቡድን ሲሆን ሁለት ጊዜ ውድድሩን በበላይነት ያጠናቀቀና የዋንጫ ባለቤት የነበረ ቡድን ነው። ይህም ውጤት የመላው ክለን ተጫዋቾችና የመላው ደጋፊ ውጤት መሆኑ ምንም ጥርጥር የለውም። ከዚህም በተጨማሪ

ኢትዮ ኮለን በፌድሬሽኑ አመራር ውስጥ ከፍተኛና ነፃ አገልግሎት በሚቻላቸው መጠን ያበረከቱ አንጋፋ ሰዎችን ለፌድሬሽኑ ያበረከተ ቡድን ነው። ከዛም በመቀጠል ቡድኑን እስከ አሁን ድረስ ደከመኝ፤ ሰለቸኝ ሳይሉ ለዚህ ያደረሱ በምሳሌነት ሊጠቀሱ የሚችሉ ሰዎችንም ያፈራ ቡድን ነው። ነገር ግን ሁሉ ነገር እንደነበረ ሊጠብቀን አይችልም፤ ጊዜ ተለዋጭ ነው፤ ነገሮችም ተለዋዋጮች ናቸውና ሰዎችም በተለይም አመራር ነን ባዮች ራሳችንን ከሁኔታዎች ጋር ማስተካከልና ሃላፊነታችንን በተገቢውና ብዙሃኑን ባካተተ መልክ ተፈፃሚነት እንዲኖረው ማድረግ ግድ ይላል፤ የወከለንን ህብረተሰብ ሆደ ሰፊ በመሆን ማዳመጥ፣ መስማትና በሃላፊነታችን መኖሩ ግንባር ቀደም ተግባራችን መሆን ይገባዋል። በእርግጥም ፍፁም መሆን አይቻልም፤ ሁሉን ማስደሰት አይቻልም፤ ነገር ግን ነፃ ግልፅና ሁሉን ያካተተ የአሰራር መንገዶችን ግን መፍጠር ይቻላል፤ ግድም ይላል። አለበለዚያማ በሃላፊነታችን መኖር ሳይሆን ሃላፊነታችንን ለራስ የተመቻቸ፣ መጠቀሚያ ማድረግ ይሆናልና ሃላፊነታችንን ሚዛናዊነት ያዘለና ለብዙሃኑ በተመቻቸ መልኩ ይሁን እንላለን።

## የኢትዮ ኮለን ወቅታዊ ጉዳይ ምን ላይ ደረሰ?

በ21/04/2013 ዓ.ም ከቡድኑ ተጫዋቾች የአመራር አካሉን የአሰራር ድክመትና ግልፅ ያልሆነ የአሰራር ችግር በተመለከተ ቅሬታና አቤቱታ መቅረቡ የሚታወቅ ነው። ይህንንም ሁኔታ በወቅቱ የኢትዮ ኮለን አመራርና ተወካይ ለነበረው ለአቶ አንዋር ሚፍታ የተገለፀና ይህንንም ቅሬታና ችግር ራሳቸው ተጫዋቾቹን በመሰብሰብና በማነጋገር ውጤቱን በቅርቡ እንደሚያሳውቅ ቃል የገባ መሆኑ የሚታወቅ ሲሆን የዚህንም ቅሬታ ውጤት በ28/04/2013 ፓልቶክ ስብሰባ ላይ በመገኘት ስለ ሁኔታው ማስረዳቱ የሚታወቅ ነው። በገለፃውም፤ ጉዳዩም በሽማግሌ የተያዘና ቀጥሎም ውይይት ማድረጋቸውንና በሜይ መጨረሻ(26/05/2013) ምርጫ ለማድረግ መስማማታቸውን መግለፁ የሚታወቅ ነው። ይህንንም ጉዳይ ፌድሬሽኑ ሲከታተል የቆየና ምርጫውም ከላይ በተጠቀሰው ቀን እንደሚደረግ አረጋግጦ ነበር። ይሁን እንጂ ምርጫው በዕለቱ የተደረገ ቢሆንም ነገር ግን በወቅቱ የነበረው የስራ አመራር አካል አቶ አንዋር ሚፍታና አቶ ሐይሌ ንጉሴ በስብሰባው ላይ ያልተገኙ መሆኑን ከተሰብሳቢዎቹ በዕለቱ መገለፁንና ምርጫውም በዕለቱ በተገኙት አባላት መካሄዱን አዲስ የስራ አመራር ኮሚቴ መመረጡን አሳውቀዋል፤ገልፀዋል። ስማቸውም፤

| ስም ዝርዝር | የስራ ድርሻ |
|---|---|
| ተስፋዬ አበበ | ሊቀ መንበር |
| ዮናስ አየለ | ምክትል ሊቀ መንበር |
| ሉቃስ ደቻሳ | ፀሐፊ |
| ዳንኤል ተሾመ | ገንዘብ ያዥ |

ናቸው። በአንፃሩም ለቦርዱ ምርጫ ለማድረግ ተስማምተናል ብሎ ቃል ከገባው አመራር አካል ማለትም ከአቶ አንዋር ሚፍታ ምንም ምላሽ ሳይገኝ መሰንበቱንና በመጨረሻም የፌድሬሽኑን ስራ አመራር ኮሚቴን ምንም ግምት ውስጥ ባለማስገባት በቀጥታ ለቦርዱ በእርሱ ዘንድ ያለውን ውሳኔ ማስተላለፉ የሚታወቅ ነው። ይህም የሚያሳየው በእርግጥም የአሰራርን ችግር ወይንም ድክመትን ነው። አጠቃላይ ጉባኤው (ምልዐተ ጉባኤው) እንዲሰራለት ያመነበትን የስራ አመራር አካል እውቅና ያለመስጠት ማለት አጠቃላይ ገባኤውን ያለማክበር ማለት ነው። እንደ አንድ ግለሰብ የስራ አመራሩን ድክመት በተገቢው ቦታና ሰዓት መውቀስ ወይንም መገሰፅ ይችላል፤ ነገር ግን የአሰራሩን አካሄድና ቅደም ተከተል መከተል ግን ግድ ይላል፤ ለራስ በተመቸ መንገድ ብቻ መጓዝ አይቻልም ብዙሃንን በሚያካትት ስራና ሂደት ውስጥ ራስን ተቀዳሚ አድርጎ ማቅረብ ተቀባይነት አይኖረውም፤ ወይንም እራሴ በምፈልገው መንገድና አካሄድ እጓዛለሁ ማለትም አይቻልም፤ በማህበራዊ ህይወት ውስጥም ቦታ አይኖረውምና ሳንወድ በግድ የብዙሃንን ምርጫ መቀበል ግዴታችን ይሆናል፤ አለበለዚያ ግን ከራስ በላይ ነፋስ ከሆነ ግን ከስብስብ መራቁ ይመረጣል።

በእኛ አመለካከት ምንም እንኳን ቅሬታው የቀረበበት የወቅቱ የስራ አመራር አካላት እስከዛሬ ድረስ ለቡድኑ ያደረጉት አስተዋፆ ከፍተኛ ነው ብለን ብናምንም ነገር ግን አሁን እየሄደበት ያለው መንገድ ግን ሃላፊነትን እንደ በፊቱ መወጣት የሚችል ወይንም በመወጣት ላይ ይገኛል ብለን ለማለት ግን እምነቱን አጥተናል።

**ይህንንም ለማለት ያስገደደን፤**

**በወቅቱ ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላት ስለ ጉዳዩ ክብደት ያለመስጠት ሁኔታ ሲሆን፤**

1ኛ/ ከቡድኑ ተጫዋቾች ከቀረበው ቅሬታ ባሻገር ከፌድሬሽኑ ስራ አመራር ጋር ችግሮችን መፍትሄ እንዲኖራቸው እያደረገ የነበረው ጥረት በጣም አነስተኛ ወይንም ጥረት ካለመኖሩ የተነሳ፤

2ኛ/ ለጠቅላላው ጉባኤ ሲፈፅም ወይንም ሲፈፅሙ ቃል የተገባውን (ምርጫ) ላይ ባለመገኘታቸው ወይንም ጉዳዩን ካለማሳወቀቸው የተነሳ፤

3ኛ/ ችግሮችን ለመፍታት አሻሚ ወይንም አስቸጋሪ ሁኔታዎች ይኖራሉ ተብሎ ቢገመት እንኳን ይህንን ለፌድሬሽኑ የስራ አመራር ጽ/ቤት ማሳወቅና አማራጭ መንገዶችን እንዲፈለጉለት ካለማድረግ የተነሳ፤

4ኛ/ የፌድሬሽኑን ስራ አመራር ተወካይ ልክ ገለልተኛና ታዛቢ በመሆን ሁኔታዎችን በሚገባ የሚገመግምበትን መንገድ የተሰጠ አማራጭን ካለመጠቀም የተነሳ፤

**ከዚህም በተጨማሪ በ16/06/2013 የፌድሬሽኑ ስራ አመራር ኮሚቴ ሁኔታዎችን በጥልቅ ከተመለከተ በኃላ ሁለቱንም ጎራ በማሰባሰብ ለማነጋገርና በጋራ መፍትሔ ለመፈለግ ያደረገው የስብሰባ ጥሪ ላይ አቶ ኃይለ ማርያም ንጉሴ አገር ውስጥ እንደማይኖር የገለፀና ነገር ግን ሌሎች ተወካዮች እንዲገኙ አደርጋለሁኝ በማለት ያሳወቀና ነገር ግን ጉዳዩን በሚገባ ሲከታተል የነበረው አቶ አንዋር ሚፍታ ያለምንም ምክንያት በስብሰባው ላይ ሳይገኝ ቀርቷል። በሁኔታውም የፌድሬሽኑ ስራ አመራር ኮሚቴ ያልተደሰተና ይህም ከአመራር ነኝ ባይ አካል የሚጠበቅ ስራ አለመሆኑንና እንደነዚህ ዓይነት የአሰራር ድክመቶች በእጅጉ መታረም እንደሚገባቸው ፌድሬሽኑ በዚሁ አጋጣሚ በጥብቅ ሊያሳስብ ይወዳል።**

**በአንፃሩ** ቅሬታውን አቅራቢው አካል(ተጫዋቾቹ) በተባለው ሰዓት በመገኘት ስለ ጠቅላላው ሁኔታና አካሄዳቸው ገለፃ አድርገዋል። ቃላቸውን ጠብቀው ቃል በገቡት መሰረት የጀርመን ህግ በሚያዘው መሰረት ግዴታችንን ተወጥተናል ብለዋል ምርጫም ተደርጎ አዲስ የስራ አመራር ኮሚቴ መመረጡንም አሳውቀዋል፤ ይህም ጉዳይ ለመመለከታቸው ክፍሎች የተላከና መልሱንም በመጠበቅ ላይ እንደሚገኙ አሳውቀዋል። በአስተያየታቸውም ላይ ፍላጎታቸው የተበጣጠሰች ሳይሆን አንድ የሆነችና ጠንካራ ኮለንን በጋራ መገንባት እንጂ ሌላ ምንም ከበስተጀርባው የሌለ ስብስብ መሆኑን ለፌድሬሽኑ የገለፁና ዛሬም ለሰላምና ለአንድነትና በጋራ ሆነው የሚጓዙበት መንገድ ከተፈጠረ ምንም ችግር እንደሌለባቸውና ወደፊትም ከማንም ጋራ ለኮለን ጥንካሬና ዕድገት በጋራ ለመስራት ዝግጁ መሆናቸውን አረጋግጠዋል።

**በእኛ አመለካከትና ግምገማ፤**

1ኛ/ ጥያቄያቸው የስልጣንና የቦታ ጥያቄ ያለመሆኑን ገምግመናል፤
2ኛ/ ከአመራሩም ጋር በጋራ በመነጋገር መስራት መፈለጋቸውን ገምግመናል፤
3ኛ/ የኢትዮ ኮለንን ቡድን የበለጠ የማጠናከር ጥረት እንዳለ ገምግመናል፤
4ኛ/ አሁንም ቢሆን ቅሬታ ከቀረበባቸው አካላት ጋር ለመወያየትና ልዩነታቸው እንዳለ ሆኖ ኢትዮ ኮለንን በጋራ የማሳደግ ፍላጎት እንዳላቸው ገምግመናል፤
5ኛ/ ብቃትና ችሎታ በጣም ከፍተኛ የመስራትና አገልግሎት የመስጠት ፍላጎት እንዳለ ገምግመናል፤
6ኛ/ በእኛ ግምገማ ኮለን በቂ ተጫዋቾች ማፍራት የምትችል ከተማ ነች ብለን እናምናለን፤ ለዚህም ምስክርነት በቅርቡ በጀርመን ዓመታዊ ውድድር ላይ በመገኘትና በመሳተፍ ማሳየት ችለዋል፤

**ይህም በመላው ተሳታፊ የጀርመን ቡድኖች ድጋፍን አግኝተዋል።**

## ውሳኔ፤

ሰዎች እንደመልካችን አስተሳሰባችን የተለያየ ነው። እነዚህም የሃሳብ ልዩነቶች ያሉና ወደፊትም የሚኖሩ ናቸው። ልዩነቶች ሊጠቡና ሊፈቱ የሚችሉት በመነጋገርና በመወያየት ብቻ ነው። ልዩነቶች እንዳሉም ሆነው በጋራ ለጋራ ዓላማ መስራትም ይቻላል። በማህበራዊ ህይወት ውስጥ የግል ፍላጎትንና አስተሳሰብን

ማንፀባረቅ ተገቢ አይደለም፤ በማህበራዊ ህይወት ውስጥ ብዙ የተለያዩ አስተሳሰቦችና አመለካከቶች ይንሸራሸራሉ። እነዚህ የሚንሸራሸሩ ሃሳቦች ሁሉ ትክክል ናቸው ማለት አይቻልም፤ ተመሳሳይ ሊሆኑ አይችሉም፤ ምንም እንኳን የራስን ሃሳብ ተቀባይነት እንዲኖረው ማድረግ ፍላጎቱ ቢኖርም ነገር ግን የብዙሃኑን ስሜትና ፍላጎት መጠበቅ ግድ ይላል።

በእኛ አመለካከት የኮለን ቡድን **አመራር** ከፌድሬሽኑ ጋር ያለው ግንኙነት እየሻከረና እየቀዘቀዘ የመጣ ለመሆኑ ጥርጥር የለንም። ይህንንም ያልንበት ምክንያት ከላይ በተዘረዘሩት ምክንያቶች ባሻገር በቅርቡ በስዊዘርላንድ አገር በተደረገው አጠቃላይና ወሳኝ ስብሰባ ላይ መሳተፍ ያለመቻል በአመራሩ ላይ ግልፅ ያሆነ ችግር እንዳለ የሚያመለክት ነው። ከዚህም በተጨማሪ **በ10/06/2013 በቁጥር: 075/ESCFE/2013** የፌድሬሽኑ ስራ አመራር የጠራውን ስብሰባ አለመገኘት ወይንም ምላሽ ያለመስጠት በራሱ ትልቅ የአሰራር ችግር እንዳለ የሚያሳይ ሆኖ አግኝተነዋል። ይህም በመጀመሪያ የፌድሬሽኑን የስራ አመራሩን እውቅና ያለመስጠት ሲሆን በሌላው መልኩ ደግሞ የስራ አመራሩን መራጭ አካል የፌድሬሽኑን አጠቃላይ ጉባኤውን ያለማክበር ነው ብለን እናምናለን።

**በመጨረሻም ከላይ በተዘረዘሩት አሳማኝ ምክንያቶች የተነሳ የፌድሬሽኑ ስራ አመራር ኮሚቴ ከዚህ የሚከተለውን ውሳኔ ለመውሰድ ተገዷል፤ አሳልፏል።**

**በአቶ ተስፋዬ አበበ የሚመራው መላው ኮለንን አቀፍ ቡድን፤**

**1ኛ/ በወጣቶችና በእውነተኛ የስፖርት ስሜት ላይ ያተኮረና የተገነባ ስለመሆኑ ገምግመናል፤**
**2ኛ/ ጥያቄ የስልጣንና የቦታ ጥያቄ ያለመሆኑን ገምግመናል ፤**
**3ኛ/ ከአመራሩም ጋር በጋራ በመነጋገር መስራት መፈለጋቸውን ገምግመናል፤**
**4ኛ/ የኢትዮ ኮለንን ቡድን የበለጠ የማጠናከር ጥረት እንዳለ ገምግመናል፤**
**5ኛ/ አሁንም ቢሆን ቅሬታ ከቀረበባቸው አካላት ጋር ለመወያየትና ልዩነታቸው እንዳለ ሆኖ ኢትዮ ኮለንን በጋራ የማሳደግ ፍላጎት እንዳላቸው ገምግመናል፤**
**6ኛ/ ብቃትና ችሎታ በጣም ከፍተኛ የመስራትና አገልግሎት የመስጠት ፍላጎት እንዳለ ገምግመናል፤**
**7ኛ/ በእኛ ግምገማ ኮለን በቂ ተጫዋቾች ማፍራት የምትችል ከተማ ነች ብለን እናምናለን፤ለዚህም ምስክርነት በቅርቡ በጀርመን ዓመታዊ ውድድር ላይ በመገኘትና በመሳተፍ ማሳየት ችለዋል፤**
**ይህም በመላው የጀርመን ተሳታፊ ቡድኖች ድጋፍን አግኝተዋል።**

## የውሳኔ እርምጃ፤

**ስለዚህም ከላይ በላይ በተዘረዘሩት ምክንያቶች በአቶ ተስፋዬ አበበ የሚመራው የኮለን ቡድን ብቻ ከፊታችን ከ17 — 20 / 2013 በሚደረገው የ11ኛው የኢትዮጲያውያን ስፖርትና ባህል ፌስቲቫል ላይ ተሳታፊ ይሆን ዘንድ የፌድሬሽኑ ስራ አመራር ውሳኔ አሳልፏል፤ተስማምተናል። በዚህም ውሳኔ ድጋፋችሁ ከእኛው ጋር እንደሚሆን ባለሙሉ ተስፈኞች እንሆናለን።**

**ኃይላችን ሕብረታችን ነው! በሕብረትም የነገን ያልተበረዘ ጭንቅላት ማፍራት ይቻላል።**

**በአውሮፓ የኢትዮጲያውያን ስፖርትና ባህል ፌድሬሽን ጽ/ቤት**

**ESCFE:** Post bus 56924, 1040AX AMSTERDAM, The Netherlands KvK (registration nr.): Amsterdam, 3432528
Tele: 0031622749520 / www.escfe.org / www.escfe.net. Bank COMMERZ BANK AG,
Kontonumber: 3303062, BLZ: 500 400 00, IBAN: - DE43 5004 0000 0330 3062 00.